# የነፃነት ትግል ከዲሞክራሲ መብቶች ጥያቄ ይበልጣል

ዳኛቸው ቢያድግልኝ

የአንድ ሀገር ሕዝብ የዲሞክራሲ ጥያቄ ሲጠይቅ የሚያነግበው መፈክር በነጻ መደራጀት፣ ሀሳብን በነጻነት መግለጽ፣ መሰብሰብና ከቦታ ወደ ቦታ ያለገደብ መዘዋወር መቻል እንዲሁም መሪዎቹን በነጻነት የመምረጥና ከስልጣን የማውረድ፣ የሕዝቡ በፖለቲካና በኢኮኖሚው መስክ እኩል ተሳትፎ ማድረግ፣ የሰብዐዊ መብት ማክበርና ማስከበር የመሳሰሉት ናቸው። ለዲሞክራሲ የሚደርግ ትግል  የምንለው ብዙ ጊዜ የአምባገነን መንግስታት የሚያሳድሩትን አገር አቀፍ ተጽእኖ የመታገያ መንገድን ነው ። እኛ ከዚህ ጥያቄም እልፍ ያልን ይመስለኛል። እኛ የጠላትነት ዓላማ ያላቸው በትውልድ ኢትዮጵያዊ ነን የሚሉ ነገር ግን በማንኛውም መመዘኛ ኢትዮጵያዊነት የሌላቸው ይበልጡንም የቅኝ ገዢዎችን ባህሪይ የሚያመላክቱ ተግባራትን ለበርካታ አመታት በማን አለብኝነት፣ ያለፍርሀትና ሀፍረት በሚተገብሩ ፍጡሮች እየተገዛን ነው። ስለዚህ ነጻነቱንም አገሩንም የተነጠቀ ሕዝብ ስለዲሞክራሲ ሲጠይቅ መቀናጣት ነው የሚሆነው። ከአውሬ መንጋጋ ሰው ስጋ ሲወሰድ ያየሁት ሐረር ካሉ ለማዳ ጅቦች ብቻ ነው። ጅቦቹ ከመንጋጋቸው ስጋው ተነጥቆ ሲወሰድ ዝም የሚሉትም ተመልሶ እንደሚሰጣቸው እንጂ ሰውየው እንደማይበላው ስለሚያውቁት ነው። ወያኔዎች ግን ስልጣን ከመንጋጋቸው እንዳይወጣ ስጋ የያዘውንም ስጋውንም ቀርጥፈው እየበሉ ነው። ማለትም ሀገሪቱንም ሕዝብዋንም እያጠፉ ነው። ከብርጋድየር ጀነራል ኃይሌ መለስ ጋር የማልግባባው በዚሁ በግብረ-አራዊት ምሳሌያቸው ብቻ ነው። አንበሳና ነብርን እንደምሳሌ ብንወስድ ካልተራቡ በቀር ያገኙትን የመግደል ባህሪይ ፈጽሞ የላቸውም። ለዚህም ነው አናብስቱ በቀን 16 ሰዐት የሚተኙት። ባይሆን ኖሮ የደኑን እንስሳ ሁሉ ጨርሰው እርስ በእርስ በተላለቁ ነበር። ለዚያውም ለአደን ሲወጡ ከእሪያዎች መካከል ጥቃት የማይቋቋምና ሮጦ የማያመልጥን ከለዩ በሁዋላ ነው ማደን የሚጀምሩት። ፈጽሞ በመግደል የሚደሰቱና ጉልበታቸውን የሚያባክኑ አይደሉም። ሕገ-አራዊት ከወያኔ አፈናና ግድያ ጋር ፈጽሞ ሊመሳሰል አይችልም። ነብርና የሜዳ ፍየል እኮ በአንድ ደን ውስጥ ነው የቁጥር ሚዛናቸውን ጠብቀው የሚኖሩት። ወያኔ ከአራዊቱም ባነስ ለራሱ ዘር ጥፋት የሚደግስ ነው።

ኮሎኒያሊስቶች አንድን ዘር ወደራሳቸው ቀረብ አድርገው ከስልጣኑና ከትርፍራፊው እየሰጡ ጀሌ እንዲሆኑ ያደርጋሉ። ወያኔዎችም የነርሱ ጋሻ ጃግሬና አፋሽ አጎንባሽ እየሆኑ በሚያገለግሉት ከትግራይ ሕዝብ በወጡ ሆዳሞች ጉያ በመግባት ወደሚጓጉበት የጥፋት አቅጣጫ ወገኔ የሚሉዋቸውን እየነዱዋቸው ነው። ወይም አንዳንዶች እንደሚሉት የታላቋ ትግራይ ችግኝ ማቆጥቆጧ ሊሆን ይችላል። *[የመስፋፋት ዘመቻው ለዚህ ምልክቱ ይሆን ይሆን?]* ከሰሞኑ የሚነበቡትና በኢንተርኔት የመወያያ መድረኮች የሚነገሩት፣ እንዲሁም በየአካባቢው የሚነፍሰው ዐየር አደገኛ ሽታ በውስጡ አለ። በቃን የሚል!!

ወያኔዎች በሩዋንዳና ቡሩንዲ የሁቱና የቱትሲ ዝርያዎችን ፈረንጆቹ እንዳደረጉት ነው እየሰሩ ያሉት። ሩዋንዳ ውስጥ በቁጥር አናሳ የሆኑትን ቱትሲዎችን የበላይ አድርገው ሁቱዎችን አሳንሰው ከኖሩበት አካባቢና ቀዬ እያፈናቀሉ አናሳዎቹ አዛዥና ጉልበተኛ ሆነው እንዲቆዩ አመቻቹ። በመጨረሻም ለቱትሲዎቹ የጥላቻና የቂም መርዝ አከርመውላቸው በሁቱዎች እንዲጨፈጨፉ ነገሮችን አመቻችተው ግዳይ ሲጣል ለማየት ዳር ቆሙ። የፈረንጅ የሀይማኖት አባቶች ሳይቀሩ በጭፍጨፋው እጃቸው ስለመኖሩ መረጃዎች በግልጽ ያሳያሉ።  የአለም ታላላቅ ኃይሎች የተባበሩት መንግስታት ድርጅትንም ጨምሮ ጆሮ ዳባ ልበስ ብለው ወደር የሌለው የዘር እልቂት ሲፈጸም ከዳር ቆመው ተመለከቱ። *[ኢትዮጵያውያን ለሰላማዊ ጥሪያቸው ምላሽ ካላገኙ ምን ሊፈጠር ይችል ይሆን?]* የሩዋንዳ ቁጥቋጦዎችና ዛፎች፣ ጅረቶችና ወንዞች በሙሉ የቱትሲዎችንና ከቱትሲዎች ጋር በሰላም መኖር የመረጡትን ፈረንጆችና 'ሞደሬት' የሚሉዋቸውን ሁቱዎች ደም ተጎንጭተዋል። *[በኢትዮጵያም የተደረጉ የዘር ጥፋቶችን እንግሊዝና አሜሪካ አልተቹበትም እንዲያውም የዲሞክራሲ ሊቆች የፀረ ሽብር አጋሮች እያሉ ወያኔዎችን ይደግፏቸዋል። ይህ በሕዝቡ ምላሽ ማግኘት ቢጀምርና ራሱን ለማዳን ጥቃት መሰንዘር ቢጀምር የዛሬዎቹ ገዢዎችና ደጋፊዎቻቸው ምን ሊሆኑ ነው?]*

በደቡብ አፍሪካ የአፓርታይድን ሥራ እንግሊዝና አሜሪካ ለበርካታ አመታት  አይቶ እንዳላየ አልፈውታል። በደቡብ አፍሪካ በተለይም በሲ አይ ኤ አባል ጠቋሚነት ማንዴላ ከታሰረ በሁዋላ ሕዝቡ የዲሞክራሲና የእኩልነት ጥያቄ ሳይሆን የነጻነት ጥያቄ በማንሳት በመጀመርያ የአፓርታይድ መሳርያ ሆነው የሚያገለግሉ ጥቁር ሰላዮችንና ወታደሮችን እጅግ አሰቃቂ በሆነ መንገድ መቅጣት ሲጀምሩ ነው ከፍተኛ መደናገጥ የተፈጠረው። በማንዴላ ላይ ሊፈጸም የነበረውን የሞት ፍርድም በመጨረሻዋ ሰዐት ያስለወጡት እንግሊዝና አሜሪካ ሲሆኑ ምክንያታቸውም የዲሞክራሲና የሰብዐዊነት ጉዳይ አሳስቦአቸው ሳይሆን ነገሮች ወደከፋ ደረጃ ሊለወጡ እንዲሚችሉ በመስጋትና ለዚህም ማንዴላ ጥሩ መያዣና መደራደርያ እንደሚሆን በመምከር ነበር። *[ብርትኳንም መያዣ ትሆን ይሆን?]* በነሁ የሚስጥር ድርድሮች መካከል ማንዴላ አስደንጋጭ እውነት ተናግሮ

እንደነበር ይነገራል። ይህም የሕዝብ ቁጥር ማደግንና በዚያም ምክንያት የሚከተለውን አደጋ ነበር። እንደሚታወቀው የነጮች ቁጥር እያሽቆለቆለ ነው። የጥቁሮች ብዛት ደግሞ እያደገ ነው። ቁጣው በዚያው መጠን እየመረረ በመሆኑ ሁኔታዎች ካልተለወጡ ዘግናኝ እልቂት በነጮች ላይ ሊፈጠር እንደሚችል ማሳሰቡ ነበር። በጥቁር ሰላዮችና በነጮችም ላይ ጭምር የቅጣት በትር መሰንዘር ተጀመረ። የመንደር ሰላዮችን ጎማ በአንገታቸው እያጠለቁ በቁማቸው ሲያቃጥሏቸውና ቅጣቱ የነጮቹንም መንደር ሲጎበኝ የአደጋው እውነታ እየታየ መጣ። *[ኢትዮጵያውያን ሆድ አደሮች አንገት ውስጥ ጎማ አጥልቀው እስኪያቃጥሉ ድረስ እየተጠበቀ ይሆን?]*

ለአፓርታይድ ገዢዎች በተነገረው መሰረት ከሃያ ስድስት አመታት እስር በሁዋላ ማንዴላ የዋስትና መደራደርያ ሆኖ ያለ ምንም ገደብና እቀባ በነጻ ተለቀቀ። በደቡብ አፍሪካ ያጠላው አደጋ በዚህ ተቋጨ። የደቡብ አፍሪካ ነጮች ከሀብትና ንብረታቸው ሳይፈናቀሉ ለጥቁሮቹ የዲሞክራሲ መብት ተሰጣቸው። ለዚህ የድርድር ውጤትም ማበረታቻ ይሆን ዘንድ ለማንዴላ የኖቤል ሽልማት ተበረከተላቸው። ጥቁር አፍሪካውያን ግን ነጻ ወጡ ለማለት አያስደፍርም። ምክንያቱም ነጮች የሚገቡበት ሆቴል ለመግባት ጥቁሮች የገንዘብ አቅም ሊኖራቸው ይገባል። ስለዚህ የቀለም ልዩነት ገድቦት የነበረውን መብት የገንዘብ ልዩነት ከቦታው መለሰው። በትግል ዘመን ስላልተማሩ የስራው እድል ክፍት እንኳ ቢሆን ተወዳድረው ነጮችን ማሸነፍ ባለመቻላቸው የነጻነቱ እልልታ ዘላቂ ደስታን ሊሰጣቸው አልቻለም። ሀገሪቱ በነጻነት ስም በሮቿ ወለል ብለው ስለተከፈቱ በመላው አፍሪካና በምስራቅ አውሮፓ ያሉ ትምህርቱና ልምዱ ያላቸው ሰዎች ያለውን ስራ ተቀራመቱት። *[ምናልባት በዲሞክራሲ መብቶች መከበርና በእርቀ ሰላም ድርድር ወያኔዎቹ የዘረፉትን ሀብት አስከብረው በነበራቸው ጊዜ ጥሩ ትምህርት ቤቶች ያስተማሩዋቸው ልጆቻቸው ኢኮኖሚውንና የመንግስት መዋቅሩን እንዲቆጣጠሩ መንገድ እያበጁ ይሆን?]* መጠነኛ ጥቁሮች የፖለቲካ ባለስልጣናት የቱጃሮቹን መንደር ተቀላቀሉ ድህነትና ኤድስ የጥቁሮችን ቁጥር የሚገድብ መሳርያ ሆኖ አረፈው። *[አንዳንድ ሰዎች የ ኤች አይ ቪ ቫይረስ የላቦራቶሪ ውጤት ነው ሲሉ ይደመጣል። የደቡብ አፍሪካ ሕዝብ ደግሞ ዋንኛው ተጠቂ ነው።]* በቅርቡ እንደታዘባችሁት የደቡብ አፍሪካ ጥቁሮች ቁጣቸውን በጥቁር ስደተኞች ላይ በማንሳት በትግሉ ዘመን መጠጊያ ሰጥተዋቸው የነበሩ ነገር ግን በአምባገነኑ መሪ ምክንያት ቀን የጣላቸውን የዚምባብዌ ጎረቤት ስደተኞችን ጨፈጨፉ። ኢትዮጵያውያንም እጣው ደርሶአቸው ነበር። ድርድሩ የፖለቲካ ስልጣንን እንጂ የኢኮኖሚውን ጉዳይ ያልነካ በመሆኑ የተፈጠረ ችግር ነው። *[በሩዋንዳና በደቡብ አፍሪካ የአገራዊ እርቅ ሸንጎ ፈስሰው ያላለቁ እንባዎችን በእርቀ ሰላም ጉባዔ ላይ ጨርሰው ጥላቻና ክፋትን ወደሁዋላ ለመተው እየሞከሩ ነው።]* ይሁን እንጂ ሩዋንዳዎችም፣ የዚምባብዌና የደቡብ አፍሪካ ሕዝቦችም ሀገርና መንግስት ስለአላቸው ለዲሞክራሲ መብት መታገል ይችላሉ። ነጻነቱንና አገሩን የተቀማ ሕዝብ ግን ከዲሞክራሲም ባሻገር መታገል ያለበት ለሀገሩ ህልውናና ለነጻነቱም ይመስለኛል። በስደት አለምን ያጥለቀለቀና በአለው ሀብትና ንብረት እንኳ በሀገሩ ሰርቶ መኖር የማይችል ሕዝብ፣ ዳር ድንበሬ እያለ ሲሞት የነበረ ዛሬ መሀል አገሩም ተነጥቆ ለአረብ ቱጃሮች እየተቸበቸበ በታሪኩ ለመጀመርያ ጊዜ መታወቂያ ደብተሩ ላይ ዘሩ ተጠቅሶ እየተጻፈ ገዢዎቹ እንደ ሰባ ፍሪዳ አንዴ ከአማራው አንዴ ከኦሮሞው እያማረጡ የሚያርዱበት ፋሺስታዊ ገዢ ያለው ሕዝብ ሊታገልና ሊዋደቅ የሚገባው ለዲሞክራሲ ብቻ ሳይሆን በቅድሚያ ለህልውናውና ለነጻነቱ ሊሆን ይገባል። ለነጻነት የሚደረግን ትግል የመሳርያ ክምችት፣ የጦር ብዛት አይገታውም።

እግዚአብሄር ይርዳን!

ዳኛቸው ቢያድግልኝ
biyadgelgne@hotmail.com